# ኢትዮጵያ ወዴት?
## ቢሆንታዎች




## የግኝቱ ጭብጥ

ጥር 2015


Forum for Social Studies
ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

SID
Society for International Developme

© 2015 ዓ.ም.

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) እና ሶሳይቲ ፎር ኢንተርናሽናል ዴቨሎፕመንት (SID)

## ማውጫ


መግቢያ........................................................................................................ 1

ቢሆንታዎች ምንድን ናቸው? .................................................................................... 1

ታሪካዊ ዳራና አሁናዊ ሁኔታ ................................................................................. 2

ቢሆንታ 1፤ የሐምሌ ጨለማ ................................................................................... 3

ቢሆንታ 2፤ መንገራገጭ ......................................................................................... 6

ቢሆንታ 3፡ ፀደይ ................................................................................................... 8

## መግቢያ

ያለፈው ግማሽ ክፍለ-ዘመን፣ ኢትዮጵያ ከአንድ ጊዜ በላይ በመስቀለኛ መንገድ ላይ የነበረችበት ጊዜ ነው። የ1966ቱ አብዮት ያለፈውን ሁኔታ የሻረ ክስተት ነበር። ሆኖም፣ በአብዮቱ ማግስት ብቅ ያለው አምባገነናዊ ስርዓት በኢትዮጵያ የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የነበረውን ተስፋ አጨልሞ በደም አፋሳሽ የእርስ-በርስ ጦርነት ተተካ። ይህ የጨለማ ጊዜ በ1983 ዓ.ም. የመንግሥት ለውጥን ተከትሎ የመጣውና የሕዝቦች እኩልነትን ያረጋግጣል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት አዲስ ሥርዓት ሲጀምር ያበቃለት መስሎ ታየ።

ይሁን እንጂ ይህን ለውጥ ተከትሎ የተቀረፀው ሕገ መንግሥት፣ ምንም እንኳን ለብሔር-ብሔረሰቦች መብቶች መረጋገጥ ዋስትና የሚሰጥ ሆኖ ቢታይም፣ በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅና እስከ አሁንም መፍትሄ ያልተገኘለት አጨቃጫቂ ምዕራፍ ከፍቷል። የኋላ ኋላ በሕገ-መንግስቱ በተመሠረቱት ክልሎች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እና በፌደራል ሥርዓቱ የመቆጣጠር ዝንባሌ መካከል በተፈጠሩ አለመግባባቶች ሳቢያ ከ2008-2010 ዓ.ም. በሃገሪቱ በርካታ ክፍሎች በተቀሰቀሰው አመጽ በ2010 የመንግሥት ለውጥ ሊደረግ ቻለ። ለውጡ ከፈጠረው ከፍተኛ የሕዝብ ፈንጠዝያ ጀርባ ግን በለውጥ አቀንቃኞችና በቀድሞው ሥርዓት ናፋቂዎች መካከል ውስጥ ውስጡን ውጥረት ሰፍኖ ነበር። ይህ የኢትዮጵያ ቢሆንታ ፕሮጀክት በዚህ በፈነጠቀው አዲስ ተስፋ ወቅት ተጠንስሶ፣ ብዙም ሳይቆይ በመጣው የነውጥ ጊዜ የተጠናቀቀ ነው። ፕሮጀክቱ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (ኤፍ. ኤስ. ኤስ.) እና በሶሳይቲ ፎር ኢንተርናሽናል ዴቨሎፕመንት (ሲድ) መካከል በ2013 ዓ.ም. የተደረገ ስምምነት ውጤት ነው።

ቢሆንታዎችን ማስቀመጥ በየትኛውም ሀገር፣ ፍፁም የተረጋጋ ሁኔታ ባለበት እንኳን፣ የሚያዳግት ጉዳይ ነው። እንደሚታወቀው፣ ኢትዮጵያ ደግሞ ከባድና ውስብስብ ሁኔታዎች ያሉባት አገር ናት።

ይህ ፈታኝ ሁኔታ ደግሞ የጥናት ቡድኑ ታሪካዊ ዳራውን ከመቃኘት ተነስቶ፣ ቢሆንታዎችን ወደ መቅረጽ ሲገባ በተግባር ታይቷል። በኢትዮጵያ ፈጣን የሆነ የሁኔታዎች ተለዋዋጭነት፣ ቢሆንታዎቹ በ10 ዓመት የጊዜ ገደብ እንዲወሰኑ አስገድዷል። ከዚህ ያነሰ የጊዜ ገደብ ብዙም ትርጉም የለውም፤ ከዚያ የበለጠ ደግሞ ከሐቅ የራቀ ይሆናል።

ለቢሆንታዎቹ መንደርደሪያ እንዲሆን የታሰበው የዳራ ጥናት ለክትትል እንዲያመች በማሰብ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች (ማለትም፣ ታሪካዊ-ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ እና ኢኮኖሚያዊ) ተደራጅተው በአዲስ አበባ፣ ካፒታል ሆቴል፣ ግንቦት 2 ቀን፣ 2014 ዓ.ም. በተዘጋጀ ዐውደ ጥናት ቀርበው ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን፣ በዐውደ ጥናቱ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የመጡ ሰዎች ተሳትፈዋል፦ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጡ ምሁራን፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራትና የግል ዘርፍ ተወካዮች እንዲሁም ወጣቶች።

## ቢሆንታዎች ምንድን ናቸው?

ቢሆንታዎች ከአንድ ሀገር ነባራዊ ሁኔታዎች ተነስቶ ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ አማራጭ ሁኔታዎችን የሚያስቀምጡ ትንተናዎች ናቸው። ጥሩ ቢሆንታዎች በጥልቅ ጥናትና ምርምር ላይ ተመሥርተው ከተለያዩ ግለሰቦች በተገኙ ሐሳቦች የሚዳብሩ ናቸው።

ቢሆንታዎች አንድ ሀገር ልትጋፈጣቸው ግድ የሚሉ፣ ወይንም ሳይከሰቱ የማይቀሩ ተብለው የሚገመቱ የዕጣ ፈንታ መግለጫዎች ብቻ ሳይሆኑ አንገብጋቢ እና የማይታወቁ ሁኔታዎችን ለይተው በማውጣት፣ መፃኢ ሁኔታዎቹ በምን አይነት ሁኔታ ወይንም በምን ይዘትና ቅርፅ ሊገለጡ እንደሚችሉ ማብራሪያ ይሰጣሉ። ቢሆንታዎች በመተባበርና በመማማር መንፈስ በሚካሄዱ የምክክር ሂደቶች እና በተፈጥሮ ብሩህ አእምሮና ንቃተ-ህሊና ካላቸው ግለሰቦች በሚገኙ ሐሳቦች የሚቀመሩ ሲሆን፣ በአንገብጋቢ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ጠቃሚ ውይይት እንዲካሄድ ያነሳሳሉ።

በአሁኑ ሰዓት፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ ውሉ በጠፋና ተለዋዋጭ በሆነ ጊዜ ላይ ትገኛለች። በሁሉም ደረጃ ላይ ያሉ የአመራር አባላት፣ ለዐሠርት ዓመታት ለዘለቁ የፖለቲካ ችግሮች ጊዜውን የዋጀ እና ዘላቂ መፍትሄ ፍለጋ ላይ ናቸው። ይህ በዕውቀትና መረዳት ላይ የተመሠረተ መፍትሄ እና አቅጣጫ ይበልጡኑ አስፈላጊ የሆነው፣ የአፍሪካ መሪዎችና ፖለቲከኞች የሕዝቦቻቸውን ተአማኒነት ባጡበት በአሁኑ ጊዜ ነው። ይህ አስከፊ ሁኔታ፣ ማኅበረቦችን አቅመ-ቢስ ያደረገውና የልማት ግቦቻቸውን ለማሳካት የሚያደርጉትን ጉዞ ያጨናገፈ የአምባገነንነት አመራር ያመጣው የከሸፈ ፖሊሲ ውጤት ነው።

በአንድ ማኅበረሰብ የመንግሥት ተአማኒነት እየተሸረሸረ ሲሄድ፣ ማኅበረሰባዊ ትስስር ሲመነምን እና በሕዝብ ዘንድ የፍትህ መጓደል/ተበዳይነት ስሜቶች ሲያንዣብቡ፣ ፅንፈኝነት ይነግሳል። እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች በአሁኒቷ ኢትዮጵያም የሚታዩ ችግሮች ናቸው። በመሆኑም ፖለቲካ መግባባትን ማሳካት ከምንም ጊዜ በላይ አሁን አስፈላጊ ነው። በኃይል ሳይሆን በዲሞክራሲያዊ መንገድ ፖለቲካዊ ስምምነት ላይ የመድረስ ችሎታ የአንድ ሀገር የእድገት ጉዞን ለማሳካት የመጀመርያው ወሳኝ ጉዳይ ነው።

ባለፉት አምስት ዐሠርት ዓመታት አብዛኛውን ጊዜ ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ ውስጥ የፖለቲካ ችግሮችን በሰላምና በውይይት የመፍታት ልምድ አልታየም። በአህጉሪቱ የአምባገነናዊ አገዛዝና የአሓዳዊ ፖለቲካ ፓርቲዎች መግነን እና የተማከለ አስተዳደር ሰፍኖ መቆየት ማኅበረሰብ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ሁኔታዎች ላይ የመደራደርና ሀብትን የመጋራት ተፈጥሮአዊ አቅምን አዳክሟል። የቢሆንታ ሂደቶች፣ ለውይይት ያሉትን መልካም አጋጣሚዎችና ክህሎቶች ስለሚያዳብሩ ለዚህ ሁኔታ አንድ ምላሽ ናቸው። ከዚህ ቀደም በአህጉሪቱ የተካሄዱ እንዲህ ዓይነት ሂደቶች ዜጎች የወደፊት አቅጣጫቸውን መልክ ለማስያዝ በግልና በጋራ እንዲመክከሩ አመቺ ሁኔታዎችን ፈጥረዋል።

ተግዳሮትም ተስፋም ፈቷ ለተደቀኑባት ኢትዮጵያ ቢሆንታዎች ምናልባትም በዚህ የአሰሳና የፍለጋ ጉዞ የመጀመሪያው እርምጃ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ጥናት ሦስት ቢሆንታዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብሎ ተገምቷል፡- **የሐምሌ ጨለማ**፣ **መንገራገጭ**፣ እና **ፀደይ**። የቢሆንታዎቹ ማጠንጠኛ ሐሳብ **በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ያለው ለውጥ አቅጣጫው ምን ሊሆን ይችላል? መቋጫውስ?** የሚል ነው። ረቂቅ ቢሆንታዎቹ ከኅዳር 23 እስከ 25፣ 2015 ኩሪፍቱ (ቢሾፍቱ) በተደረገ ዐውደ ጥናት ላይ ቀርበው በውይይት ሊዳብሩ ችለዋል። እነሆ አሁን ለወሳኝ አካላትና የአገሪቱ ዕጣ ፈንታ ያገባናል ለሚሉ ባለድርሻ አካላት ሁሉ ግብዓት ይሆናሉ በሚል እምነት ቀርበዋል።

## ታሪካዊ ዳራና አሁናዊ ሁኔታ

### *ታሪካዊና ባህላዊ*

የኢትዮጵያ አገረ መንግሥት ለዘመናት የሚያስደንቅ ጽናትን ለማሳየት ችሏል። ያጋጠሙትን ፈተናዎችና ጫናዎች ተቋቁሞ ቅርጹ እየተለዋወጠ ነገር ግን መሠረታዊ ማንነቱን ሳይለቅ ዘልቋል። በቅርብ ጊዜ የብሔረሰብ ማንነት መግነንን ተከትሎ የተከሰቱት ግጭቶችና የማዕከላዊው መንግሥት መዳከም በኢትዮጵያ አንድነት መቀጠል ላይ ጥያቄ አጭሯል። ሦስት ቢሆንታዎች ይታያሉ፡- መበታተን፣ ተፎካካሪ ኃይሎች የገነኑበት የተዳከመ አገራዊ አንድነት፣ እና የተጠናከረ አገራዊ አንድነት። ከዚህ ጋር በቅርብ የሚቆራኘው ጉዳይ ላለፉት ሦስት ዐሠርት አወዛገቢ ሆኖ የቆየው የማንነት ጥያቄ ነው።

ኢትዮጵያ የሁለቱ ዐቢይ ሃይማኖቶች፣ የክርስትና እና እስልምና፣ ሀገር ናት። ሁለቱም ከመጀመሪያው ሺህ ዓመታት (ሚሌኒየም) ጀምሮ የቆዩ ነባር ሃይማኖቶች ናቸው። በ16ኛው መቶ ዓመት ከተከሰተው አውዳሚ የርስ በርስ ጦርነት በስተቀር በሰላም አብረው ቆይተዋል። የኦርቶዶክስ እምነትና ጴንጠቆስታሊዝም እምብዛም ባይጋጩም የጎሪጥ ሲተያዩ ኖረዋል። በዚህ ታሪካዊ ዳራ መሠረት ምን ዓይነት ቢሆንታ ልንጠብቅ እንችላለን?

የአፍሪቃ ቀንድ የጠብና ግጭት ቀጣና መሆኑ ይታወቃል። ለበላይነት የሚደረግ ፉክክር፣ የድንበር ውዝግብ፣ የግዛት ይመለስልኝ ጥያቄና የሕዳሴው ግድብ ለውጥረቱ መስፈን በየፊናቸው አስተዋጽኦ አድርገዋል። ይሁን እንጂ የቀጣናው ሕዝቦች የተዛመዱና የተጋመዱ ናቸው። የዚህ ውጥረት የሰፈነበት ቀጣና ዕጣ ፈንታ ምን ይሆን?

### *ፖለቲካዊ*

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ፈላጭ ቆራጭነት የሰፈነበት ነው። ፈላጭ ቆራጭነት የፖለቲካ ባሕሉ መገለጫ ሆኖ ቆይቷል። ለዚህ ባህል መንሰራፋት አስተዋጽኦ ያደረጉት የኢትዮጵያ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ አደረጃጀቶች ከላይ ወደ ታች ወራጅና አባታዊ መሆን ናቸው። በፖለቲካዊ ኃይሎች ዘንድ ሰጥቶ የመቀበል ባህል አለመዳበር እና እርባና ያላቸው መዋቅራዊ ለውጦችን ለማድረግ አለመቻል ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመሥረት እንቅፋት ሆነው ቆይተዋል።

ከዚህ ባሻገር ደግሞ በሀገሪቱ የሰፈነው ግጭት ውስብስብ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። በጥቅምት 2013 በትግራይ ክልል የተጀመረው ጦርነት ወደ አማራና አፋር ክልሎችም ተዛምቶ በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ዜጎች ሞትና መፈናቀል ምክንያት ሆኗል። በተጨማሪም በምዕራብና ማዕከላዊ ኦሮሚያ መንግሥት ሸኔ ብሎ የሚጠራውና ሽብርተኛ ብሎ የፈረጀው የኦሮሞ ነፃ አውጪ ሠራዊት ለረጅም ጊዜ ያካሄደው አመፅ አለ። በሌሎች የሀገሪቱ ክልሎችም ውጥረትና ግጭት ሠፍኗል፤ በቀድሞው የደቡብ ክልል፣ ክልል ልሁን የሚለው ጥያቄ፣ በሌሎች ደግሞ በግዛትና በሀብት ዙሪያ የሚደረጉ የይገባኛል ጥያቄዎች ይታያሉ።

በአጠቃላይ፣ ብሔረሰብን መሠረት ያደረገው ፌዴራሊዝም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ አጨቃጫቂው ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። ሙስና መረን ለቆ ከቁጥጥር ውጭ ሆኗል። ለዚህም ሁኔታ ዋነኛው ምክንያት በባለሥልጣናት፣ በነጋዴዎችና በደላሎች መካከል ያለው ሽርክና ነው ተብሎ ይገመታል።

### *ኢኮኖሚያዊ*

ኢትዮጵያ በዓለም ካሉ ድሃ አገሮች አንዷ ናት። እርሻ የኢኮኖሚዋ ዋልታ ሲሆን፤ በነፍስ ወከፍ ግማሽ ሄክታር የነበረው የመሬት ይዞታ እያሽቆለቆለ ይገኛል። ግጭትና የተፈጥሮ ቀውስ ተዳምረው በአምራች የሰው ኃይልና በኢኮኖሚያዊ እሴቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል። በሌላ በኩል፣ ከ1983ቱ የሥርዓት ለውጥ በኋላ በተለይ በመሠረተ ልማትና በጂዲፒ ዕድገት ረገድ አዎንታዊ ለውጥ ታይቷል። አንዳንድ የመንግሥት ተቋማትን፣ በተለይም ትላልቅ ኮርፖሬሽኖችን፣ ወደ ግሉ ዘርፍ የማዛዋወር ሂደትም ተጀምሯል። ይህ ሂደት በተለይ ከ2010ሩ የመንግሥት ለውጥ በኋላ የታወጀው የ"አገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም" አካል ሆኖ ተጠናክሮ ቀጥሏል።

የአየር ንብረት ለውጥ በኢኮኖሚው ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽእኖ አሳሳቢ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። በዘልማድ በየካቲትና ሚያዝያ መካከል የበልግ ዝናብ የሚያገኙት አካባቢዎች የሚያገኙት የዝናብ መጠን በ16% ቀንሷል። ይህም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ በሠፈረበት በስምጥ ሸለቆ አካባቢ ከፍተኛ የምግብ እጥረት አስከትሏል። በመኸር ዝናብ በሚያገኙት አካባቢም ቢሆን፤ የዝናቡ መጠን መቀነስ የአካባቢውን ሕዝብ ለችግር ዳርጎታል። በደቡባዊ-ማዕከላዊና በምሥራቅ ደጋማ አካባቢዎች የተከሰተው የሰብል መጠን መቀነስ የአካባቢውን ሕዝብ ኑሮ ከማቃወሱ አልፎ በአጠቃላይ የእህል ዋጋ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል።

ሌሎች አሳሳቢ ጉዳዮች ደግሞ እያደር ከቁጥጥር ውጭ እየሄደ ያለው የዋጋ ግሽበት፣ ሥራ አጥነት እና እያሽቆለቆለ የሚሄደው የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ከ120 ሚሊዮን በላይ ሲሆን፣ ይህም ከአፍሪቃ ሁለተኛውን ደረጃ ይዟል። ዓመታዊ የሕዝብ ብዛት የመጨመር መጠንም 2.5% ነው። ይህን የሕዝብ ጭማሪ ትሩፋት ለመጠቀም በሰው ሀብት ዕድገት ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ይጠይቃል።



# ቢሆንታ 1፤ የሐምሌ ጨለማ

*የመበታተን አደጋ*

አስደንጋጭ ቢሆንም፤ የአገሪቱ የመበታተን አደጋ የማይታሰብ ነው ማለት አይቻልም። ምንም እንኳን በማዕከላዊው መንግሥትና በሕወሃት መካከል የተቀሰቀሰው ጦርነት በሰላም የተቋጨ ቢመስልም፤ የሕወሃት አጋር ድርጅት የሆነው የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች፣ አንዳንዴም ከዋና ከተማዪቱ አዲስ አበባ ብዙም ሳይርቅ፣ የጦር እንቅስቃሴውን ቀጥሎ ኦሮሞ የሆኑትንም ያልሆኑትንም ሰለባ ማድረጉን ቀጥሏል። ገዥው የብልጽግና ፓርቲም ቢሆን አንድ ወጥ ቁመና አለው ብሎ መናገር ያስቸግራል። በዘመነ ኢሕአዴግ እንደታየው፤ የፓርቲው የተለያዩ አካላት አማራ ብልጽግና፣ ኦሮሞ ብልጽግና፣ ወዘተ፣ እያሉ ለተለያየ ማንነታቸው አጽንኦት መስጠት ጀምረዋል። የወደፊቱ ጦርነት በአማራና በኦሮሞ መካከል ሊሆን ይችላል የሚል ከባድ ስጋትም አለ።

መሠራች ድርጅቶቹ የተለያየ ማንነታቸውን ከማጉላትም አልፈው የዘመነ መሣፍንትን በሚያስታውስ መልኩ የራሳቸው የደረጀ ሠራዊት ማሰማራት ጀምረዋል። ስለሆነም የፖለቲካ ልዩነቶች ወደ ጦር ማማዘዝ ካደጉ አገሪቱ ወደ አስከፊ የርስ በርስ ጦርነት እንዳትገባ ያሰጋል። ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ባለፈው ታሪኳ የተለየ ጽናት ብታሳይም፤ ይህ ሁልጊዜ ሊቀጥል ይችላል ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ያዳግታል። ዜጎች በገፍ እየተገደሉ መንግሥትም ይህን ለማቆም ባልቻለበት ሁኔታ የአገሪቱ ቀጣይነት አጠራጣሪ ቢሆን አይገርምም።

ከፖለቲካ ልዩነቶችም ባሻገር የሃይማኖት ልዩነቶችም ተከስተዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የትግራይ ቅርንጫፍ ከእናት ቤተ ክርስቲያኗ ለመለየት እንቅስቃሴ የጀመረ ሲሆን፤ የተለየ የኦሮሞ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋምም ጥረት ሲደረግ ተመልክተናል። በቅርቡ አል ሸባብ ከሶሞሊያ ወደ ኢትዮጵያ ሰርጎ መግባት ለጊዜው ቢገታም በሌላ መልክ ቀጥሎ ቀጣናውን ወደ አለመረጋጋት ሊመራ ይችላል።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ምክንያት ማዕከላዊው መንግሥት ተናግቶ የመንደር አባ ወራዎች ወይም የጎበዝ አለቃዎች የበላይነት ሊያገኙ ይችላሉ። የአሁኑን የክልል ድንበር መሠረት በማድረግም ነፃ መንግሥታት ሊቋቋሙ ይችላሉ። ሁኔታውን ይበልጥ ውስብስብ የሚያደርገው ደካማና የተከፋፈለች ኢትዮጵያን እንደ ዘላቂ ጥቅማቸው የሚያዩ የውጭና አጎራባች አገሮች ጣልቃ ገብነት ነው።

## *የብሔረሰባዊ ማንነት መክረር*

ብሔረሰባዊ ማንነት ሥር ከመስደዱ የተነሣ እንዲሁ በዋዛ የሚታለፍ አይሆንም የሚል አጠቃላይ ግንዛቤ አለ። እሱን መሠረት ያደረጉ ክልላዊ መንግሥታት ከነገዢ ልሂቃቻቸው ጋር ተፈጥረዋል። እነዚህ ልሂቃንም የማንነት ጥማታቸውን ለማርካት ሳይሆን ያገኙትን ሥልጣንና ጥቅም ለማስከበር ሲሉ ይሞቱለታል። ከመጀመሪያውም ቢሆን የራስን ዕድል በራስ መወሰን የሚለው መርህ በብሔረሰባዊ አርነት ንቅናቄዎች ዘንድ ገኖ ሊወጣ የቻለው በአንደኛ ደረጃ ሕዝባቸውን ከኋላቸው በማሰለፍ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የበላይነት ለመጨበጥ ሁነኛ መሣሪያ ሆኖ ስላገኙት ነው ማለት ይቻላል።

በጥቅምት 2013 በትግራይ የተቀሰቀሰው ጦርነትና እሱንም ተከትሎ የተፈፀሙት የጦር ወንጀሎች የትግራዋይ ማንነትን ከመቼውም በበለጠ ሁኔታ አክርሮታል። ባንፃሩም በአፀፋው ሕወሃት በአማራ ክልል ያደረሰው ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት የአማራን ብሔረሰባዊ ማንነት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ አሳድጎታል። ይህ ስሜት በተለይ ፋኖ ተብሎ በሚታወቀው ኢመደበኛ ሠራዊት ዘንድ ጎልቶ ይታያል። በዚህ ሂደትም የ2010ሩ የመንግሥት ለውጥ መሠረት የነበረው የኦሮ-አማራ ኅብረት ፈተና ላይ ወድቋል። ይህን ውጥረት ያባባሰው ደግሞ በኦሮሞ ክልል የሚገኙ አማሮች የኦሮሞ ነፃ አውጪ ሠራዊት ባደረሰባቸው የጅምላ ጭፍጨፋ ምክንያት መፈናቀላቸውና ይህንንም ለመግታት የፌዴራል መንግሥቱም ሆነ ክልላዊ መንግሥቱ ይህ ነው የሚባል እርምጃ አለመውሰዳቸው ነው።

በዚህ ቢሆንታ የክልላዊ መንግሥታት ነፃነት እየገነነ የፌዴራል መንግሥቱ ሥልጣን እየኮሰመነ ይሄዳል። ይህን ቢሆንታ ገሃድ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁለት ሁኔታዎች አሉ። አንደኛው ሕገ መንግሥቱ ለክልሎች የሚሰጠው ሰፊ የውስጥ ነፃነት ነው። ሁለተኛው በብሔረሰብ ማንነት ላይ የተመሠረተው የኢትዮጵያ ፌዴራል ሥርዓት ነው። የፌዴራል መንግሥቱ የዜጎችን ደኅንነት የማስጠበቅ አቅሙ እየሰለለ ሲሄድ፤ ብሔረሰባዊ ንቅናቄዎች ይህን ክፍተት ከመሙላትም አልፈው የኅብረተሰባቸውን ደኅንነት እንጠብቃለን በሚል ሰበብ የፌዴራል መንግሥቱን ሥልጣን ከመሻማት ወደኋላ እንደማይሉ ይገመታል።

## *የሃይማኖት ግጭቶች*

በሚቀጥለው ዐሠርት የሃይማኖት ግጭቶች በተደጋጋሚ ሊከሰቱ እንደሚችሉ አንዳንድ አስደንጋጭ ምልክቶች ይታያሉ። ለዚህም በማስረጃነት የሚጠቀሱት በቅርቡ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የታዩ ኹነቶች ናቸው። ሞጣ በታኅሣሥ 2012፣ ጎንደር በሚያዝያ 2014 የአንድ የተከበሩ የሙስሊም ሼክ የቀብር ሥነ ሥርዓትን ተከትሎ፣ ወዲያውኑም በአዲስ አበባ ተቀጣጠለ። እነዚህ የማይገናኙ የሚመስሉ ኹነቶች በማህበራዊ ሚዲያ አራጋቢነት የሚባባሱ የሃይማኖት አክራሪነቶች (ክርስቲያንም ሙስሊምም) ነፀብራቅ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። በተለይም የሃይማኖት በዓላት የሃይማኖት ግጭቶች መነሾ መሆናቸው እየተለመደ መጥቷል።

## *በአፍሪቃ ቀንድ የሚታየው ግጭት መባባስ*

አል ሸባብ የተባለው የሶማሊያ ጂሃዲስት ቡድን አጎራባች አገሮች (ኬንያ እና ኡጋንዳ) ላይ ያደርስ የነበረውን ጥቃት በማስፋት ወደ ኢትዮጵያም መዝመት ጀምሯል። የትግራይ ጦርነት በድኅረ-2010 በአዲስ ተስፋ የተጀመረው የኢትዮጵያና ኤርትራ ግንኙነት ላይ አጥልቶበታል። የኤርትራ ዓላማ ሕወሃትን ለአንዴም ለሁሌም ማጥፋት ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ግን በኅዳር 2015 የተፈራረመችው የጦርነት ማቆም ውል እንደሚያመለክተው ነገሩን በሰላም የምትቋጭበት አስገዳጅ ምክንያቶች አሏት። ይህ ስምምነት የፕሬዚዳንት ኢሳይያስና የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን ግንኙነት በማሻከር በሁለቱ መካከል ተፈጥሮ የተነበረውን ወዳጅነት ሊያላላው ይችላል። ሌላ ሊጠበቅ የሚችለው ቢሆንታ ደግሞ በድኅረ-ኢሳይያስ ኤርትራ ልትከተለው የምትችለው ፖሊሲ ነው። አሁን ፈጽሞ የማይታሰብ ቢመስልም የትግራይ-ኤርትራ ጥምረት ተፈጥሮ ኢትዮጵያን በብርቱ ሊፈትናት ይችላል።

የሰሜኑን ጦርነት በማስታከክ የሱዳን ጦር በታኅሣሥ 2013 ወደ ኢትዮጵያ ይዞታ ዘልቆ መግባት በሁለቱ አገሮች የድንበር ውዝግብ ታሪክ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል። ከዚህ ጋር የሚያያዘው ደግሞ በሕዳሴ ግድብ ዙሪያ በኢትዮጵያ

እና በሱዳንና ግብፅ መካከል የተፈጠረው አለመስማማት ነው። በተለይ የግድቡ ፍጻሜ አይቀሬ እየሆነ ሲመጣ፤ ግብፅ ያለ የሌለ ኃይሏን በኢትዮጵያ ውስጥ አለመረጋጋት በመፍጠር ላይ ተጠምዳ ቆይታለች። ኢትዮጵያ የሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ ኃያል መንግሥት ሆና፣ ግብፅ ሁለተኛ ደረጃን መያዝ አትፈልግም።

### *የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ*

በመጪው ዐሠርት ዓመት፣ በኢትዮጵያ ፈላጭ ቆራጭ አደጋ አይኖርም ማለት አይቻልም። የአገሪቱ ነባር የፖለቲካ ባህል፣ የፖለቲካ መሪዎች የመቻቻልን ጥበብ ማዳበር አለመቻላቸውና አስፈላጊ የሆኑ መዋቅራዊ ለውጦች አለመከናነወናቸው ለዚህ ዓይነት አዝማሚያ የሚያግዙ ናቸው። በ1966ም ሆነ በ1983 ዓ.ም. በተደረጉት ለውጦች የፖለቲካ ምኅዳሩ ከሰፋ በኋላ ወዲያውኑ ጠቦ የፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት ሰፈነ። አሁንም በ2010 የፈነጠቀው የዲሞክራሲ ተስፋ ጭላንጭል ሥር በሰደደው የአገሪቱ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ባህል ላለመዋጡ ምንም ዋስትና የለም። የመሪዎችን ሥልጣን የሚገድቡ ተቋማት አልዳበሩም። የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችም ቢሆኑ የመንግሥትን ፈላጭ ቆራጭ አዝማሚያ ለመገደብ አቅማቸው ገና አልፈረጠመም። ሌላው ይህንኑ አዝማሚያ የሚያጠናክረው ጉዳይ በብሔረሰባዊ ክፍፍል ምክንያት አገር-አቀፍ ጥምረት ለመመሥረት አለመቻሉ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የፖለቲካ ሽግግሩ የፈጠረውን አለመረጋጋት ለመቆጣጠር ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ አይቀሬ ነው የሚል እሳቤም አለ። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች፣ በዚህ ሁሉ ምክንያት በድኅረ-2010 የተከፈተው የፖለቲካ ምኅዳር እየጠበበ ሄዶ መንግሥት እንደ ተለመደው ተቃዋሚ ኃይሎችን፣ በተለይም ሚዲያውን፣ ማፈን ጀምሯል። የመንግሥት ሚዲያም ከሞላ ጎደል የመንግሥትን አቋም የሚያስተጋቡ ሆነዋል። በእንዲህ ያለ ድባብ፣ በግለሰብ ዙሪያ የሚሽከረከር ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ የሚጠበቅ ቢሆንታ ነው።

### *የፍጹም ድኅነት መንሰራፋት*

ያለፉት መንግሥታት ሰላማዊና አካታች የልማት ሥርዓት ለመዘርጋት እንቅፋት የሆኑትን ሁኔታዎች በማስወገድ ዘላቂ የሆነ የኤኮኖሚ ዕድገትና ልማት ለማምጣት ዝግጁነት አልታየባቸውም። መጠነ ሰፊ ግጭትና የልማት ዕቅዶችን ማስፈጸም አለመቻል ለኢኮኖሚ ዕድገት ማነቆ ሆነው ቆይተዋል። የሰሜኑን ጦርነት ተከትሎ አገሪቱ ከአጎዋ ታገኝ የነበረውን የቀረጥ ነፃ ዕድል መነጠቋ፣ የአውሮፓ ኅብረት ለመንግሥት ያደርግ የነበረውን የበጀት ድጎማ ማቋረጥ የውጭ ምንዛሪ እጥረቱን ይበልጥ አባብሶታል። ሥራ አጥነት፣ በተለይም በወጣቱ ዘንድ፣ እያደገ መሄዱ አይቀሬ ነው። እነዚህ አሉታዊ ሁኔታዎች የድኅነት መጠኑን ያባብሱታል። ከድኅነት ወለል በታች የሚኖረው ሕዝብ ቁጥር አሁን ካለው 23.5% ከፍ ሊል ይችላል።

### *የአየር ንብረት ለውጥ መባባስ*

ሊገመቱ በማይችሉ ሁኔታዎች ምክንያት በሚቀጥሉት ዐሥር ዓመታት ማናቸውም የአየር ንብረት ለውጥ ሉላዊ የማስታገሻ ዒላማዎች ሊሳኩ አይችሉም። ስለሆነም፣ የተራዘመ ጎርፍና ከባድ ድርቅ የተፈራረቁበት ፈታኝ የአየር ንብረት ለውጥ ሊከሰት ይችላል፤ ይህም በኤኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ጫና ያደርሳል። ብሎም የብዙ ሕዝብ መፈናቀልንና ፍልሰትን ሊያስከትል ይችላል።

### *የዋጋ ግሽበት*

የዋጋ ግሽበቱ በአሁኑ ሁኔታ ከቀጠለ አንድ ሰው አሁን በ1000 ብር ለሚገዛው ዕቃ ከአንድ ዓመት በኋላ 1400 ብር ለመክፈል ይገደዳል። ደላሎች ትርፉን እያጋበሱ ገበሬውንና የከተማውን ድሃ ይበልጥ ያደኸዩታል። የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር አለመቻሉም ሙስናን ያባብሳል፤ ምክንያቱም ሙስና አንዱም የሚመነጨው እየናረ የሚሄደውን የዕቃዎች ዋጋ ለመቋቋም ካለው ፍላጎት ነው። ይባስ ብሎም በብራዚልና ቺሊ በ1960ዎቹ እና በ1970ዎቹ እንደታየው አይነት የመንግሥት መውደቅ ሊኖር ይችላል።



# ቢሆንታ 2፤ መንገራገጭ

ሁለተኛው የታለመው ቢሆንታ የአገሪቱ ችግሮች የተወሳሰቡ በመሆናቸው ምክንያት ብዙም ለውጥ ሳይታይ የአሁኑ ሁኔታ መቀጠል ነው። ምንም እንኳ በሕወሃትና በፌዴራል መንግሥቱ መካከል የሰላም ስምምነት ቢፈረምም፤ አንዳንድ አጨቃጫቂ ጉዳዮች አሁንም እልባት አላገኙም። ከነዚህም መካከል ተፃራሪ የይገባኛል ጥያቄ ያላቸው የወልቃይት (ምዕራብ ትግራይ) እና የራያ ጉዳዮች ናቸው። የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት በኦሮሚያ ክልል የፈጠረው አለመረጋጋትም መቀጠሉ አይቀርም።

መንግሥት የዋጋ ግሽበትን ለመግታት የሚወስዳቸው እርምጃዎች ከማስታገሻ የዘለሉ አይደሉም። የባለሥልጣኖች በጉዳዩ ተጠቃሚ መሆን ማንኛቸውንም የቁጥጥር እርምጃ ያመክነዋል። ስለሆነም ግሽበቱ እየቀጠለ ሄዶ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት በጣም አስቸጋሪ ያደርገዋል። በተጓዳኝም፣ ሙስናን ለመቆጣጠር አዳጋች ይሆናል።

### *ያልተማከለ ፈላጭ ቆራጭነት*

በዚህ ቢሆንታ ክልሎች ዐቢይ ሚና የሚጫወቱበት የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ይፈጠራል። ማዕከላዊው መንግሥት እየተንገዳገደም ቢሆን ይቀጥላል፤ ነገር ግን በክልሎች ላይ ያለው ሥልጣን የሰለለ ይሆናል። ትንሽም ነፍስ የሚዘራው የፌዴራል ሠራዊቱ በሚያደርግለት ድጋፍ ነው።

### *የብሔረሰባዊ ፌዴራሊዝም መቀጠል*

የፌዴራል ሥርዓቱ ጥቂት ማሻሻያ ተደርጎለት ይቀጥላል። አለመረጋጋት የመፍጠሩ ሁኔታ ለዘብ ብሎ ብሔረሰባዊነት የፌዴራሊዝም ማጠንጠኛ መሆኑ ይቀጥላል። በአዲስ ክልል፣ ዞን፣ ወዘተ ለመደራጀት የመጠየቁ ሁኔታ፣ ከዚያም ባለፈ በግዛትና ማንነት ጉዳይ በአዋሳኝ ክልሎች መካከል ያለው ውዝግብ ውጥረትና ግጭትን ያስከትላል። በየክልሉ የሚኖሩ ንዑሳን ብሔረሰቦችም መብታቸውን ተነፍገው በብሔረሰቦች መካከል ያለው ግንኙነትም እንደሻከረ ይቀጥላል። በሦስቱ ታላላቅ ክልሎች - ኦሮሚያ፣ አማራ እና ትግራይ - መካከል ያለው ግንኙነትም ውጥረት የሞላበት ሆኖ በመቀጠል የአገሪቱን አለመረጋጋት ያባብሰዋል። ክልሎች ማዕከላዊ መንግሥቱን ባያስወግዱም የውስጥ ነፃነታቸው ግን እየጎለበተ ይሄዳል። እስከ መገንጠል ለመሄድ የማይገፉበት ምክንያት ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት አዳጋች በመሆኑ ነው።

### *በብሔረሰባዊ ማንነትና በኢትዮጵያዊነት መካከል ያለው ውጥረት መቀጠል*

ብሔረሰባዊ ማንነት ለሚቀጥሉት ዓመታት ገኖ እንደሚቀጥል ይጠበቃል። በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያዊነት ስሜት ብርቱ ፈተና ይገጥመዋል። ስለሆነም በቅርቡ ጎልቶ ይወጣል ብሎ ለመገመት ያዳግታል። በብሔረሰባዊ ማንነት ላይ የተመሠረተውን የፌዴራል አወቃቀር ለማፍረስ የሚደረግ ማናቸውም ሙከራም መዘዙ ሌላ ዙር አመፅ ይሆናል። አገዛዙ

ቅቡልነትን ለማግኘት ብሔረሰባዊ ማንነትንና ኢትዮጵያዊነትን እንደ አመቺነቱ እያጣቀሰ ይቀጥላል። በሌሎች ክልሎች የሚኖሩና የሚሠሩ ዜጎች የሚያጋጥማቸው ችግርም መፍትኄ አያገኝም። በዚህ ሁሉ ምክንያት ብሔረሰባዊ ማንነትን በኢትዮጵያዊነት ለማረቅ የሚደረገው ሙከራ ሊሳካ አይችልም።

### *በሃይማኖቶች መካከል ያለው ውጥረት መቀጠል*

የለየለት የሃይማኖት ጦርነት ባይከሰትም አሁን ያለው ውጥረት ይቀጥላል። ሙሉ በሙሉ ወደ ጦርነት የማይሄድበት ምክንያት እስካሁን ያለው ውጥረት የተበታተነ እና ወቅታዊ እንጂ አጠቃላይ እና ዘላቂ ባለመሆኑ ነው። የውጥረቱ ምንጭ በአብዛኛው ግለሰቦች ሁለንተናዊ ግጭት ለማምጣት የሚያደርጉት ቁስቆሳ በመሆኑ ነው።

### *የአፍሪቃ ቀንድ ሁኔታ*

በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል የተፈጠረው አዲስ ወዳጅነት ለሁለቱም ጠቀሜታ ስላለው ሙሉ በሙሉ ሊቀለበስ ይችላል ብሎ ለማመን ይከብዳል። በኢትዮጵያና ሶማሊያ መካከል ያለው ግንኙነትም ለክፉም ሆነ ለበጎ ትልቅ ለውጥ ያሳያል ብሎ ማሰብ አይቻልም። የአል ሸባብ ወደ ኢትዮጵያ ሰርጎ መግባት መጀመር አዲስ ክስተት መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ በሌላ በኩል ምናልባትም የቡድኑን ውድቀት ሊያስከትል ይችል ይሆናል። በ1969 ለሶማሊያ የመስፋፋት ፖሊሲ መስፈንጠሪያ የነበረችው ኦጋዴን አሁን አሁን የኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት መገለጫ እየሆነች መጥታለች።

ኢትዮጵያና ሱዳን በሕዳሴው ግድብ ምክንያት ወደ ለየለት ጦርነት ይገባሉ ብሎ ማሰብ ያዳግታል። ሱዳን በታኅሣሥ 2013 ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ያደረገችው መስረግ ኢትዮጵያ በወቅቱ በትግራይ ጦርነት መጠመዷን አይታ ያደረገችው ጊዜያዊ እርምጃ እንጂ የዘላቂ ስትራቴጂ አይመስልም። አሁን የገባችበት ቀውስም እንዲህ ዓይነት ጀብደኛ እርምጃ ከመውሰድም ያግዳታል። የሕዳሴ ግድቡም በኢትዮጵያና በሱዳንና ግብፅ መካከል የጦርነት መንስዔ መሆኑ እጅግ አጠራጣሪ ነው። ለነገሩ ሱዳን በግድቡ ላይ ያላት ተቃውሞ እንደ ግብፅ የከረረ አይደለም። ግብፅም ብትሆን በአንድ ወቅት ከፍታ የነበረውን የዲፕሎማሲ ዘመቻ ገታ አድርጋለች። ሦስት ዙር የውሃ ሙሌት ከተከናወነ በኋላ የግድቡ ጉዳይ ያለቀለት ይመስላል። በሙሌቱ ምክንያት ይመጣል የተባለው ጉዳትም አልታየም። ከአሁን በኋላ የግብፅ ስጋት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ብቻ ዓላማው ከሆነው ግድብ ይልቅ ኢትዮጵያ የዐባይን ውሃ ለመስኖ እርሻ እንዳትጠቀምበት ይሆናል።

### *የኢኮኖሚው ሁኔታ*

የዋጋ ግሽበቱ በፈጠረው የኤኮኖሚ ችግር ምክንያት ሕዝቡ ያምፃል ብሎ ማሰብ ስለሚያዳግት አሁን ያለው ሁኔታ ያለምንም ለውጥ ሊቀጥል ይችላል። ኢኮኖሚው አንዳንድ መሻሻሎች ቢያሳይም፣ ኢንቬስተሮችና ሌሎችም የኢኮኖሚው ተዋናዮች ባደረባቸው ጥርጣሬ ምክንያት ዕድገቱ ቀርፋፋ ሊሆን ይችላል። ለሚቀጥሉት ዐሥርት ዓመታት፣ አገሪቱ ድኅነት የሰፈነባት፣ የነፍስ ወከፍ ገቢው ዝቅተኛ የሆነባት፣ በውጭ እርዳታ ላይ ጥገኛ እንደሆነች ትቀጥላለች።

የመሬት ስሪት ሁኔታም ውስብስብ ከመሆኑ የተነሣ ወደ ግል ይዞታ ይዘዋወራል ብሎ መገመት ያዳግታል። እንደዚያ ዓይነት እርምጃ የመሬት ሽያጭን በማስከተሉ ኢፍትሐዊ ውጤት ሊያመጣ ይችላል። ለነገሩ መሬትን ወደ ግል ይዞታ የመቀየሩ ጉዳይ የብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች አጀንዳ አይደለም።

### *ትላልቅ የመንግሥት ኢንተርፕራይዞችን ወደ ግል ይዞታ የማዘዋወሩ ሂደት*

በቅርቡ መንግሥት ትላልቅ ኢንተርፕራይዞቹን ወደ ግል ይዞታ የማዘዋወር ዝንባሌ እያሳየ መጥቷል። የውጭ ምንዛሪ እጥረት እና የፕሪቶሪያው ስምምነት ከምዕራባውያን መንግሥታት ጋር የፈጠረው መቀራረብ ይህን ሂደት ሊገፋፋው ይችላል። ይሁን እንጂ ፖሊሲው የራሱን ችግር ይዞ የሚመጣ ነው። የሥራ አጥነት መስፋፋትና እሱም የሚያስከትለው ኢፍታሓዊነት መንግሥት በፖሊሲው እንዳይገፋበት ሊያደርገው ይችላል።

### *የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም አለመቻል*

አብዛኛው የአገሪቱ ክፍል እርጥበት ስለሚሰፍንበት የእርሻ ምርት በመጨመሩ ድርቅ በሚያጠቃቸው አካባቢዎች የሚከሰተውን የዝናብ እጥረት ሊያካክስ ይችላል። ይሁን እንጂ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚወሰዱ እርምጃዎች አመርቂ አይደሉም። አሁን የሚታየው የድርቅና ጎርፍ መፈራረቅ ይቀጥላል። በዚህ ሁሉ ምክንያት አሁን ያለው የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተጽእኖ በቀላሉ አይገታም።

### *የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር ስኬታማ ፖሊሲ አለመኖር*

የኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት መዋቅራዊ በመሆኑ ከተለመደው የፍላጎት/አቅርቦት ሞዴል ወጣ ያለ ፖሊሲ ይፈልጋል። የአገሪቱ ኢኮኖሚ ዓይነተኛ ባሕርያት ኋላ ቀርና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ እርሻ፣ ደካማ ተቋማት፣ የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ አለመጠቀም እና የማያባራ ግጭት ናቸው። የዋጋ ግሽበት ኢኮኖሚውን ተጣብቶታል ማለት ይቻላል። እነዚህን መዋቅራዊ ችግሮች በአጭር ጊዜ መፍታት ስለማይቻል የዋጋ ግሽበቱ ይቀጥላል ተብሎ ይገመታል።



# ቢሆንታ 3፡ ፀደይ

### *እንደገና ማንሰራራት*

በሦስተኛው ቢሆንታ ኢትዮጵያ የተጠናወቷትን ችግሮች አስወግዳ እንደገና የምታንሰራረበት ነው። የተጋረጡበት ችግሮች መፍትኄ አልባ ሊመስሉ ይችላሉ። የረጅም ጊዜ ታሪኳ ሲጤን ግን ያን ያህል አይበገሬ አይደሉም። መፍትኄው የሚመጣው ሕዝቧ በአገሪቱ ጽናት ላይ ያለው እምነትና አንድነቷን ለመጠበቅ በቁርጠኝነት የሚቆምና ብዝኃነቷን የሚመጥን ብሔራዊ ሠራዊት መገንባቱ ነው።

ሌላው አበረታች ሁኔታ ደግሞ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን መቋቋሙ ነው። ኮሚሽኑ ተልእኮውን ለመፈፀም የሚያሳየው ጥንቃቄና ዘዴ የተመላበት አካኼድ ስኬታማ ሊሆን እንደሚችል አመላካች ነው። መንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በተለይ ሲቪል ማኅበረሰቡ እና የውጭ አገር ለጋሽ ድርጅቶች፣ ለኮሚሽኑ ግብዓት የሚሆኑ ተግባራት በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

### *የኢትዮጵያዊነት ስሜት ገኖ መውጣት*

የአገሪቷ ረጅም ታሪክ የሚያመላክተው ነገር ቢኖር፣ የማታ ማታ ኢትዮጵያዊነት ገኖ እንደሚወጣ ነው። የአድዋ ድል ቅርስ፣ በሶማሊ ወረራ፣ በባድሜ ጦርነትና በቅርቡ በተከሰተው የሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ወቅት ሕዝቡ በአንድነት ሆ! ብሎ መነሳቱ የሚያመለክቱት፣ ኢትዮጵያዊነት በብሔረሰባዊ ማንነት የተዋጠ ቢመስልም አፈር ልሶ እንደሚነሳ ነው።

በ18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና የኢትዮጵያ ባንዲራ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ካደረጉት አትሌቶች መካከል ሦስቱ የተገኙት የቅርቡ የእርስ በርስ ጦርነት እምብርት ከሆነችው ከትግራይ ነው። በቀድሞ ጊዜ የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑ አትሌቶች አገሪቱን በአትሌቲክስ ማማ ጫፍ ላይ እንዳስቀመጧት ሁሉ፤ አሁን ደግሞ የትግራይ አትሌቶች አገሪቱን ወደ አዲስ ከፍታ እያወጧት ይገኛሉ። የነዚህ አትሌቶች ዘመን ተሻጋሪ ገድል የሚያመለክተው ብሔረሰባዊ ማንነት በአብዛኛው በፖለቲካ ልሂቃን የሚቀነቀን እንጂ ወደ ሰፊው ሕዝብ እንዳልሰረገ ነው።

ይሁን እንጂ አሁን የሚከሰተው ኢትዮጵያዊነት የከረረ ሳይሆን የለዘበና ለብሔረ ሰባዊ ማንነት ቦታ የሚሰጥ ነው የሚሆነው። ሁለቱ ተጻራሪ የሚመስሉ ማንነቶች ተቻችለው የሚኖሩበት ሁኔታ ነው የሚፈጠረው። የፌዴራል ሕገ መንግሥቱም የብሔረሰቦችን መብት ዕውቅና መስጠት ብቻ ሳይሆን ዜግነትን መሠረት ያደረገ አካታች ኢትዮጵያዊነትንም እንዲያፀና ተደርጎ ይሻሻላል። የክልል ሕገ መንግሥቶችም ንዑሳን ብሔረሰቦች በሰላምና በነፃነት መኖርና መሥራት እንዲችሉ ሆነው ይሻሻላሉ።

በዘር ፍጅት መካከል የሰከነ አስተሳሰብ ሊኖር እንደሚችል በመስከረም 2011 አፀፋ እርምጃ በመውሰድ የሚመጣውን አደጋ ያስቆሙት የጋሞ አባቶች አሳይተውናል። ይህ ተግባራቸው በመላው ሕዝብ ዘንድ አድናቆትንና አክብሮትን አስገኝቶላቸዋል። እንዲህ ያሉ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በጋሞዎች ብቻ የተወሰነ አይደለም። አያሌ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መሰል የግጭት መፍቻና የአስተዳደር ዘዴ አላቸው። እነዚህ እሴቶች አሁን የሰፈነውን ዘር-ተኮር ፍጅት ለማርገብ ይረዳሉ።

### *አካታችና አሳታፊ የፖለቲካ ስምምነት*

ግላዊም ሆነ ያልተማከለ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ስር እንዳይሰድ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። የድኅረ-2007 ሕዝባዊ አመፅና ውጤቱ እንደሚያሳየው ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ዘላቂ መረጋጋትን አያመጣም። ሌላው አካታች ፖለቲካን አይቀሬ የሚያደርገው ማንኛቸውም የፖለቲካ ፓርቲ ብቻውን የበላይነቱን ለመጨን አለመቻሉ ነው። ሁኔታው በምርጫ ውጤትም ሆነ ያለ ምርጫ ጥምር መንግሥት ማቋቋምን የሚጋብዝ ነው። በኢትዮጵያ በመጪው ዐሠርት ዓመት የሚመጣውን የፖለቲካ ስምምነት በመሬት ላይ ያለው የኃይል ሚዛን የሚወስነው ይሆናል። የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ ፍጹም የበላይነት ማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ ሲመጣ በገዥው ፓርቲና ተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል ድርድር መደረጉ አይቀሬ ነው። የኤኮኖሚው አሳሳቢ ሁኔታ፣ ዓለም አቀፍ ጫናና የሕዝቡም መታከት ይህን ቢሆንታ ያጠናክራሉ።

### *የሃይማኖት መቻቻል*

ከአስፈሪው የሐምሌ ጨለማ ቢሆንታ ይልቅ፣ በረጅሙ የአገሪቱ ታሪክ የታየው የሃይማኖቶች መቻቻል ገኖ ሊወጣ እንደሚችል አመላካች ሁኔታዎች አሉ። እንዲህ እንደ ቅርቡ ውጥረት በሞላበት ጊዜ እንኳን አንዳንድ አበረታች የሃይማኖቶች መቻቻል ምልክቶች ታይተዋል። ሃይማኖት-ነክ ግጭቶችን ለማርገብ ታቅደው የተቋቋሙት የበይነ-ሃይማኖት ጥምረቶችም ለዚህ በጎ አዝማሚያ አጋዥ ይሆናሉ።

### *ኅብረ-ብሔራዊ ፌዴራሊዝም*

በዚህ ቢሆንታ፣ የፌዴራል ሥርዓቱ ይቀጥላል፤ ነገር ግን አንዳንድ ወሳኝ የሆኑ ማሻሻያዎች ይደረጉለታል። የመንግሥትና ኅብረተሰብ ግንኙነት ዴሞክራሲያዊ ባሕሪ እየተላበሰ ሲመጣ ፌዴራሊዝም ያብባል፤ ያለ ዴሞክራሲ እውነተኛ ፌዴራሊዝም የለምና። ኅብረ-ብሔራዊ ፌዴራሊዝምን፣ አገራዊ አንድነትንና ዜግነትን ለማጠናከር ከሚያግዙ ማሻሻያዎች አንዱ የመገንጠል መብትን የሚደነግገውን አንቀጽ መሻር ነው። ሌላው ደግሞ ያለቅጥ የተለጠጡትን ክልሎች ለአስተዳደር ወደ ሚያመቹ አሃዶች መከፋፈል ነው። የክልሎች ይዘታ እንዲህ ተመጣጣኝ መሆኑ መረጋጋት ለማምጣት ያግዛል።

### *ቀጣናዊ ውኅደት*

ሁኔታዎች አልመቻች ብለው ነው እንጂ፣ የአፍሪቃ ቀንድ አገሮች አንድ ለመሆን በቂ ምክንያቶች አሏቸው። አብዛኛዎቹ ብሔረሰቦች ድንበር ዘለል ናቸው። በቋንቋ ከመገናኘታቸውም ባሻገር በኤኮኖሚ ተሳስረዋል። ስለዚህ ቀጣናውን በኮንፌዴሬሽን የማስተሳሰር ሐሳብ ከአንዴም ሁለቴ መሰንዘሩ የሚያስደንቅ አይደለም። በ1960ዎቹ መጨረሻ ላይ የመንግሥቱ ኃይለ ማርያምና የዚያድ ባሬ ወዳጅ የነበረው ፊደል ካስትሮ ኢትዮጵያን፣ ሶማሊያን እና የመንን በፌዴሬሽን ለማስተሳሰር ሐሳብ አቅርቦ ነበር። በቅርቡ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ኢትዮጵያን፣ ኤርትራንና ሶማሊያን የማቀራረብ እርምጃዎች ሲወስዱ ታይቷል። በግልፅ ባይወጣም ሦስቱን አገሮች በኮንፌዴሬሽን የማስተሳሰርም ዕቅድ ሐሳብ የተውጠነጠነ ይመስላል።

### *ኤኮኖሚያዊ ብልጽግና*

እ.አ.አ. ከ2010 እስከ 2019 ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛውን የኤኮኖሚ እድገት በማሳየት ብሩህ ተስፋ ፈንጥቃ ነበር። የእርሻ ምርታማነትን ማሳደግ የመንግሥት ፖሊሲ ትኩረት ካደረገባቸው ጉዳዮች አንዱ ነው። በዚህ ረገድ በቅርቡ የታየው የስንዴ ምርትን ማሳደግና በመኪና ማረስ የምግብ ዋስትናን እና አጠቃላይ ደህንነትን ለማረጋገጥ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በቢሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞች የተተከሉበት የአረንጓዴ አሻራ ፕሮጀክት የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋምና ዘላቂ ዕድገትን ለማምጣት ይረዳል።

ከዚህም ባሻገር በአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ አማካይነት አገራዊ መግባባትን ለመፍጠርና ግጭቶችን ለመፍታት የሚደረጉት ጥረቶች ለኢንቨስትመንትና ነፃ የምርት መሣሪያዎች ዝውውር ወሳኝ የሆነውን ሰላምና መረጋጋት ያመጣሉ። እንዲህ ያለው ሁኔታ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ካፒታልን ከመሳቡም በላይ የሥራ ዕድልን ይፈጥራል፤ ቴክኖሎጂያዊ ዕድገትን ያግዛል፤ ንግድን ያስፋፋል፤ የአካባቢ ጥበቃ እርምጃዎች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይረዳል። በአጠቃላይም ፈጣን የኤኮኖሚ ዕድገት ሊመዘገብ ይችላል።

### *የግሉ ሴክተር እንደ አንቀሳቃሽ ሞተር*

መንግሥት የግሉን ሴክተር በማበረታታት ውድድር ያለበት ኤኮኖሚን ለመመሥረት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ለዚህ አንዱ መንገድ የመንግሥትና የግል ሽርክናዎችን መፍጠር ሲሆን፤ እነዚህ ሽርክናዎች በትክክል ከተተገበሩ የተሻለ ውጤትና ዕድገትን ሊያመጡ ይችላሉ። የአገሪቱ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ሲሻሻሉ አሉታዊውን ዓለም አቀፍ ጫና በማርገብ ብርቅ እየሆነ የመጣውን የውጭ ምንዛሪና ኢንቬስትሜንት ያመጣል። መንግሥት አካታች የሆነ የኤኮኖሚ ሪፎርም ፖሊሲ ይከተላል፤ ውጤታማ የፀረ-ሙስና ፖሊሲና እስትራቴጂ ይተገበራል፤ በተለይ ዝቅተኛ ደሞዝ የሚያገኘውን የኅብረተሰብ ክፍል ገቢ ከማሳደግም አልፎ ኤኮኖሚውን ያረጋጋል።

### *የአረንጓዴ ልማት እንቅስቃሴ*

መንግሥት የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና እስትራቴጂዎች ተግባር ላይ አውሏል። አዳዲስ የአካባቢ ደኅንነትን ለመጠበቅ የሚረዱ የምርት ዘዴዎች ኤኮኖሚውን ጠንካራ መሠረት ላይ ለማቆም ይረዳሉ። የማክሮ ኤኮኖሚክ መረጋጋትን በተመለከተ መንግሥት የተሻለ የበጀት አስተዳደር በመተግበር፣ የንግድና የገንዘብ ፖሊሲውን በማሻሻል እና ለግጭቶች ሰላማዊ መፍትኄ በመሻት ፈታኝ እየሆነ የመጣውን የዋጋ ግሽበት ያረግባል።

**Forum for Social Studies (FSS)**
Tel. 251-0111545605/06
P.O. Box 25864 code 1000
Addis Ababa,
Ethiopia
Email: fss@ethionet.et
Web: www.fssethiopia.org.et

**Society for International Development (SID)**
Rome
Via degli Etruschi 7, 00185, Rome, Italy
TEL: +39064872172
EMAIL:sidsec.rom@sidint.org
Nairobi
6th Flr., Timau Plaza, Argwings Kodhek Road,
P O BOX 2404, 00100 Nairobi
TEL: +254-700065624
EMAIL:sidsec.nbo@sidint.org